# የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያ

**የእሁድ ፕሮግራም መርሃ-ግብር**

ህይንን ቤተ ክርስቲያን እንድንገለገልበት የፈቀዱልንን የሬቨንስ ውድ ባብቲስት ቤተ ክርስትያን የእሁድ ከሰአት አምልኮ ፕሮግራም እንዳናስተጓጉል የእሁድ ፕሮግራማችን በተመደበለት ሰአት ማስኬድ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ሽማግሌዎች የሚከተለው የሰአት አጠቃቀም በጥብቅ እንዲተገበር ወስነዋል። ጌታ ይባርካችሁ!

- **ጸሎት፡ 1:30-2፡00**
- **አምልኮ፡ 2፡00-2:30**
- **ማስታወቂያ/መባ፡ 2:30-2:45**
- **ቃል፡ 2:45-3:45**
- **የፕሮግራም ፍጻሜ፡ 4፡00**
- **የህብረት ጊዜ 4፡00– 5፡00**

**የአዲስ አመት ዋዜማ**

የአዲስ አመት ዋዜማን December 31 ከ 5 p.m. ጀምሮ እናከብራለን። ምግብ ይኖረናል፣ የጸሎትና የአምልኮ ጊዜ ይኖረናል፤ ቲሸርት ይዘጋጃል፤ የስነ-ጽሐፍ ጊዜ ይኖረናል። ስነ-ጽሑፍ ለማቅረብ የምትፈልጉ ለረድኤቱ አስታውቁ። ስዎችን ጋብዙ። ጌታ ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጻደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10

# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!




"በዚያን ጊዜ ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣህን እግዚአብሔርን እንዳትረሳ ተጠንቀቅ።"
(ዘዳ. 6:12)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**December 1, 2019** | **ሕዳር 21፤ 2012 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

**ጸሎት** ........................... ወንድም ፍቅሩ ካዩ

**አምልኮ**......................... የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

**ፕሮግራም መሪ** ............ ወንድም ጸደቀ ጴጥሮስ

**ቃል** .............................. ወንድም ሲሳይ መሸሻ

**ማጠቃለያ** .................... ወንድም ጸደቀ ጴጥሮስ

## የሳምንቱ ጥቅስ

"አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፥ እርሱም፥ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው።" (ሮሜ 3:21-22)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ሲሳይ መሸሻ | | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ኮከቤ አስረስ | | |
| ወ/ም ዘሪሁን/ዮሐንስ | | |
| ወ/ም አያሌው/ጸደቀ | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### መንፈስ ቅዱስ ወቃሽ (ገላጭ) መንፈስ።

*"እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል።" (ዮሐ. 16:8)*

መንፈስ ቅዱስ አሁን ሶስት ወሳኝ ስራዎች ያደርጋል። አንደኛ ስለ ኃጢያት አለምን ይወቅሳል። ሁለተኛ የክርስቶስን ጽድቅ ለአለም ይገልጻል። ሶስተኛ ስለ የመጨረሻውን ፍርድ ያስጠነቅቃል። በዚህ ክፍል እንደምናየው በኃጢያት እና በፍርድ መካከል የክርስቶስ ጽድቅ መካከለኛ ሆኖ አለ። ኃጢያት ወደ ፍርድ ይወስዳል ነገር ግን ከፍርድ መውጫው መንገድ የክርስቶስን ጽድቅ መቀበል ብቻ ነው።

መንፈስ ቅዱስ አለምን ስለ ኃጢያት ይወቅሳል። ይህም ሰው ኃጢያተኝነቱን አምኖ ክርስቶስን በመቀበል ይድን ዘንድ ነው። ወንጌል ሲሰበክ በክርስቶስ ኢየሱስ የማያምኑትን መንፈስ ቅዱስ ይወቅሳቸዋል። ይህ "ይወቅሳቸዋል" የሚለው ቃል መንፈስ ቅዱስ የሚሰራውን ኃጢያትን የመግለጥ ስራ የሚያሳይ ነው። ይህ የመግለጥ ስራ ደግሞ ሰው ወደ ራሱ ተመልክቶ በኃጢያቱ እንዲወቀስና ወደ ንስሃ ይመጣ ዘንድ ነው። ለዚህ ነው ሐዋሪያው ጴጥሮስ በበዓለ አምሳ ቀን ከተለያየ ቦታ መጥተው በኢየሩሳሌም ለተሰበሰቡት ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወንጌሉን በስልጣን ከሰበከ በኋላ የሰሙት ሰዎች ልባቸው ተነክቶ "ወንድሞች ሆይ፥ ምን እናድርግ?" ብለው ጠየቁ (ሐዋ. 2:37)። በዚህን ጊዜ ሰዎቹ በኃጢያታቸው እንደተወቀሱ አስተውሎ ሐዋሪያው ጴጥሮስ "ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ" አላቸው (ቁ. 38) ይህንን ቃል ከሰሙት በዚያን ቀን ሶስት ሺህ ሰዎች እንደዳኑ እናነባለን (ቁ. 41)። ቃሉ ሲሰበክ ሰዎች ኃጢያተኝነታቸው ተሰምቶአቸው እንዲወቀሱ፣ ብሎም ንስሃ እንዲገቡ ያደረገው መንፈስ ቅዱስ ነው።

መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስን ጽድቅ ይገልጣል። አሁን ጌታችን በአካል በመካከላችን የለም ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ አለ። መንፈስ ቅዱስ ጌታን ያከብረዋል። በጌታም የመጣውን የመዳን ጽድቅ ለሰዎች ሁሉ ይገልጻል። ይህም መጽሐፍ "አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፥ እርሱም፥ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው" እንደሚል (ሮሜ 3፡ 21-22) መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ያገኘነውን የእግዚአብሔርን ጽድቅ ይገልጻል። እንዲሁም ደግሞ ለኛ ለምናምን የእግዚአብሔርን ጽድቅ እያበራ በጽድቅ እንድንመላለስ አቅም ይሰጠናል። ከጽድቅም ሃሳብ ስንስት ወቅሶ ይመልሰናል። አንዳድ ጊዜ ሰዎች ጌታን ከተቀበሉ በኋላ አንዳንድ አለማዊ ልማዶችን ይዘው ይቀጥላሉ። ጥቂት ቆይተው ግን እንዲህ አይነቱን ነገር ማንም ምንም ሳይላቸው ይተውቷል። ለዚህ ምክንያቱ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስን ጽድቅ ስለሚያበራላቸው በቀደመው ሕይወት ለመቀጠል ስለማይችሉ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ሊመጣ ያለውን በሰይጣን እና በተከታዮቹ የሚፈጸመውን የመጨረሻ ፍርድ ይገልጣል። ዲቢሎስ ተፈርዶበታል። በመጨረሻ የወንድሞች ከሳሽ ይጣላል። ጠላታችን የወደቀ፣ የተፈረደበት የፍርድን ፍጻሜ የሚጠብቅ እንደሆነ በመግለጥ በጥላታችን ፊት በኃይል እንድንገለጥ የሚያደረገን መንፈስ ቅዱስ ነው። ወገኖቼ፡- የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ እየሰማን እንመላለስ። እርሱ ከኛ ጋር ነው። ስለ ኃጢያት ይወቅሳል፤ የክርስቶስን ጽድቅ ይገልጻል እንዲሁም የመጨረሻውን ፍርድ ያሳውቃል። አሜን!